# የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ምንነት እና ጥቅም

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ አንድ አውጪ እንደ አክሲዮን፣ ቦንዶች ወይም ሌሎች የፋይናንስ መሳሪያዎችን ያሉ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ ሽያጭ ለማቅረብ ወይም ቁጥጥር በሚደረግበት ገበያ ላይ ለመገበያየት ከኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ፈቃድ የሚያገኝበትን መደበኛ ሂደት ያመለክታል። ይህ ሂደት ስለ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና ስለ አውጪው ሁሉም መሰረታዊ መረጃዎች በግልጽ እና ከሚመለከታቸው ህጎች እና መመሪያዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ በምዝገባ ሰነዱ እንዲገለጹ የካፒታል ገበያ አዋጅ ያስገድዳል።

***<u>የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ዓላማ እና የቁጥጥር መሠረት</u>***

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ መስፈርቶች በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 አንቀጽ 75–78 ላይ የተመሰረቱ ሲሆን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሕዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 ላይ የበለጠ ተብራርቷል። የምዝገባው ዋነኛ አላማዎች የሚከተሉትን ያካትታል።

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ የመጀመሪያው ዓላማ የኢንቨስተሮች ጥበቃ ነው። ኢንቨስተሮች በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን ለማድረግ ሙሉ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ ኢንዲያገኙ የአውጪው ድርጅት ሙሉ ቁመና  እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ መመዝገቡ ወሳኝ ነው።

ሌላው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ የገበያ ታማኝነትን ማረጋገጥ ሲሆን በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የማጭበርበር እና አሳሳች ተግባራትን ከመከላከል ባለፈ ፍትሃዊ የሆነ የካፒታል ተደራሽነትን ያበረታታል።

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ሌላኛው ዓላማ የባለሥልጣኑን ቁጥጥር ማገዝ ሲሆን የካፒታል ገበያ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን አውጪዎችን እንዲከታተል፣ የይፋ ማድረግ ግዴታዎችን እንዲያስፈጽም እና የገበያ ዲሲፕሊን እንዲያስጠብቅ ያስችለዋል።

***<u>የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ሂደት ቁልፍ ባህሪያት</u>***

የደንበኛ ሳቢ መግለጫ(Prospectus) ግምገማ፡- አውጪዎች የፋይናንስ፣ የስጋት እና የስጋት አስተዳደር፣ እና የገቢ አጠቃቀምን የሚገልጽ ዝርዝር የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ በተሰጠው የኢንቨስትመንት ባንክ ወይም የኢንቨስትመንት አማካሪ አሰርተው ማቅረብ አለባቸው።

አውጪዎች የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በባለሥልጣኑ ማስመዝገብ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ቀጣይነት ያላቸው ግዴታዎች ወቅታዊ የፋይናንስ ሪፖርት ማድረግን ጨምሮ ድርጅቱ ውስጥ የሚፈጠሩ መሰረታዊ ለውጦች ሲኖሩ ይህንኑ ይፋ ማድረግ አለባቸው።

Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT

አዋጁ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማስመዝገብ ግዴታ አውጪው ላይ ቢጥልም እንደ የመንግስት ቦንዶች ወይም በግል ሽያጭ የሚቀርቡ የተወሰኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና ሌሎችም ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ከምዝገባ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ።

ሌላው የአውጪው ሰነዶቹን በባለስልጣኑ ማስመዝገብ ፋይዳ ወደፊት ድርጅቱን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ለመመዝገብ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚጠቅም መሆኑ ነው። የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ብቻ ፈቃድ ባላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ሊመዘገቡ ወይም ሊገበያዩ ወይም ለሕዝብ ሊቀርቡ ይችላሉ።

***<u>የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ</u>***

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በባለሥልጣኑ የማስመዝገብ ሂደት እያደገ ላለው የካፒታል ገበያ መሠረት ነው። የኢንቨስተሮችን በራስ መተማመን ያሳድጋል፣ ግልጽነትን ያበረታታል፣ እና ገበያውን ከአለም አቀፍ ምርጥ ልምዶች ጋር ያስተካክላል እንዲሁም የካፒታል ምስረታን እና የኢኮኖሚ እድገትን ይደግፋል።

ይህ ጽሁፍ የካፒታል ገበያ የህግ እና የቁጥጥር መሳሪያዎች ከሆኑት ዋነኛ ስለሆነው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ማስመዝገብ ስለሚኖረው ፋይዳ ብሎም ለአውጪዎች (Issuers) እና ለኢንቨስተሮች የሚሰጠው ጥቅም ለማብራራት ይሞክራል። በአንጻሩ በአውጪዎች ደረጃ እንደ ድርጅት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የምዝገባ መስፈርቶች ሳያሟሉ እንዲሁም የደንበኛ ሳቢ መግለጫቸውን (Prospectus) በባለሥልጣኑ ሳያስጸድቁ አክሲዮን እና ሌሎች ቦንድ እና መሰል ሰነዶችን ለሕዝብ በሚሸጡ አውጪዎች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገዥው ላይ ሊደርስበት የሚችለውን የገንዘብ ጉዳት ለመቆጣጠር ሊደረግ ስለሚገባ ጥንቃቄ እንዳስሳለን።

***<u>የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ሚና</u>***

የካፒታል ገበያ አሰራር ተዋንያኑን እና ግብይቱን ለመቆጣጠር በመንግሥት በተቋቋመ ባለሥልጣን መስሪያ ቤት ቁጥጥር ይደረግበታል። ዓለም አቀፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ተቆጣጣሪዎች ድርጅት (International Organization of Securities Commissions (IOSCO)) የካፒታል ገበያ አሰራርን በተመለከተ የቁጥጥር ዓላማዎችን በሚመለከት የተለያዩ ዓለም አቀፍ መርሆዎችን እና ደረጃዎችን በየጊዜው በማውጣት ይታወቃል። ይህ ድርጅት ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የቁጥጥር አሰራር ያወጣቸው ዓላማዎች ሶስት ሲሆኑ እነዚህም ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስተሮች ከለላ መስጠት፤ የግብይት ሥራው ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ግልጽነት የሰፈነበት እንዲሆን ማድረግ እና መዋቅራዊ የአደጋ ስጋቶችን መቀነስ ናቸው። ታዲያ እነዚህ በአለም አቀፉ ድርጅት የወጡ የቁጥጥር ዓላማዎችን ለማሳካት የተደራጀ የካፒታል ገበያ ያላቸው ሃገራት በየወሰናቸው የካፒታል ገበያ ተቆጣጣሪ ተቋም አቋቁመዋል። ወደ እኛ ሃገር ስንመጣ በሃገር ደረጃ የተደራጀ የካፒታል ገበያ የተቋቋመ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት አላማዎችን ለማሳካት፣ ገበያውን እና ተዋንያንን ፈቃድ የሚሰጥ እና የሚቆጣጠር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በአዋጅ ተቋቁሟል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
ECMAT

የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ሥልጣን እና ተግባር በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩ ሲሆን ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ፈቃድ መስጠት፣ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን ፈቃድ መስጠት፣ ፈቃድ መሰረዝ እና ማገድ፤ የሰነደ ሙዓለ ንዋይን የመመዝገብ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የሚከናወነውን የምዝገባ እና ከምዝገባ የመሰረዝ ሥራ መቆጣጠር፤ የገበያ እና ግብይት ሥርዓት ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ፤ በገበያው ተሳታፊዎች በሚሰጡ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ እንዲተሳሰሩ ማድረግ፤ እንዲሁም እነዚህን እና ሌሎች ሥራዎች ጨምሮ አዋጁን ለማስፈጸም የሚጠቅሙ ማናቸውንም መመሪያ የማውጣት ስልጣን ለባለሥልጣኑ ተሰጥቶታል።

***<u>ለሕዝብ የሚሸጡ አክሲዮኖችን ማስመዝገብ</u>***

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ከተቋቋመበት ዓላማ አንዱ በገበያው ሊያጋጥሙ የሚችሉ መዋቅራዊ የአደጋ ስጋቶችን ለመከላከል ነው። ባለፉት በርካታ አመታት በሃገራችን በሕግ እና በተቋም የሚመራ የተማከለ የአክሲዮን ገበያ ባለመኖሩ ዜጎች አክሲዮን ማህበር እናቋቁማለን በሚሉ ግለሰቦች ገንዘባቸው ተበልቶ እንደቀረ ይታወሳል።

ስለሆነም አክሲዮን መግዛት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚገዛው ድርጅት አክሲዮኖች በባለሥልጣኑ የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ድርጅቱ የሚመዘገበው የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን በማስመዝገብ ነው። የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በካፒታል ገበያ አዋጅ እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ መሠረት ባለሥልጣኑ ፈቃድ በሰጠው አካል የተዘጋጀ እና ስለአውጪው ድርጅቱ ሰፊ መረጃ የያዘ፣ የኢንቨትመንት ፖሊሲ፣ የሀብት ግመታ፣ ኦዲት ሪፖርት፣ ትርፍ፣ ዕዳ፣ ትልልቅ ኮንትራቶች ካሉት መጠናቸው፣ ኢንቨስት በሚደረግበት ዘርፍ ያሉ ስጋቶች ትንተና፣ የስጋት አስተዳደር እቅድ እና ሌሎች መሠረታዊ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘ ሆኖ አክሲዮን ማህበሩ ይህንኑ ለባለሥልጣኑ አቅርቦ ያስጸደቀ እና ያስመዘገበ መሆን አለበት። ይህ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በአይነቱ በንግድ ህጉ አንቀጽ 447 ከተገለጸው ዝቅተኛ መመዘኛዎችን ከሚያስቀምጠው መስፈርቶች በተጨማሪ ከላይ የተዘረዘሩትን ሌሎች የአክሲዮን ማህበሩ ዝርዝር መረጃዎችን የሚያካትት ነው።

ከአክሲዮን ማህበር የድርሻ ሰነድ(አክሲዮን) ሊገዛ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሁሉም አስቀድሞ ድርሻ ስለሚገዛበት ድርጅት በቂ መረጃ እና እውቀት ሊኖረው ይገባል። የአክሲዮን ማህበሩ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በባለሥልጣኑ ሲመዘገብ ለሕዝብ ይፋ የሚደረግ በመሆኑ ገዥዎች ይህንን መግለጫ በቀላሉ ሊያገኙ እና መረጃ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ነው።

ከላይ በተጠቀሱት አዋጅና መመሪያ መሰረት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪ አክሲዮን ማህበራት ለህዝብ የተሸጡና በመሸጥ ሂደት ላይ ያሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እስከ ህዳር 16 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው።

ይህን ተከትሎ ባለአክሲዮኖቻቸው ከሃምሳ በላይ የሆኑ አክሲዮን ማህበራት(የሕዝብ ኩባንያዎች) የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በማውጣት በባለሥልጣኑ ያስመዘገቡ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ምዝገባው ተጠናቋል።

የምዝገባ ሥርዓቱ የአውጪው መረጃዎችን ባለማወቅ አክሲዮን በሚገዙ ሰዎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ኪሳራ ሊያስቀር ይችላል። ይህ የምዝገባ ሥርዓት ግልጸኝነትን በመፍጠር የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያውን እና ተዋናዮቹን ከጉዳት እና ከውድቀት ለመጠበቅ ይረዳል ተብሎ ይገመታል። ምዝገባ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዋነኛው የቁጥጥር መሣርያ እንደመሆኑ ጥቅም ላይ ማዋል መሰረታዊ ጉዳይ ነው።  በመሆኑም ህብረተሰቡ የምዝገባ መስፈርቶችን ሳያሟሉ እና በባለሥልጣኑ ሳይመዘገቡ ለሕዝብ አክሲዮን ከሚሸጡ ድርጅቶች አክሲዮን በመግዛት ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል። አክሲዮን ማህበራት በባለሥልጣኑ ምዝገባ ሳያደርጉ የአክሲዮን ሽያጭ ማስታወቂያ በማንኛውም መገናኛ ብዙኃን ማስነገር የተከለከለ መሆኑ በመመሪያው በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል። በመሆኑም አክሲዮን ገዥዎች በአውጪው ድርጅት የተዘጋጀውን መግለጫ በመፈተሽ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

***<u>የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ለገዥው የሚሰጠው ጥበቃ</u>***

አክሲዮኖቻቸውን ለሕዝብ ሽያጭ የሚያቀርቡ አውጪዎች ባለሥልጣኑ የምዝገባ መግለጫውን ለመመርመርና ለማጽደቅ አስፈላጊ የሚባሉ መረጃና ሰነዶች ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይጠበቅበታል። ይህም የምዝገባ ሰነዶቹ አክሲዮኖችን ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች የአክሲዮኑን ትክክለኛ ዋጋ እንዲያውቁ ይረዳሉ። የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ግልጽነትን የሚፈጥር እና በገበያው ላይ እምነት የሚገነባ ስርዓት ነው። የምዝገባው ሌላ ጥቅም የቁጥጥር እና የድጋፍ ማዕቀፍ ማቋቋም እና ጤናማ የግብይት ሥርዓት ለመዘርጋት የሚረዳ እንደሆነ ይታመናል።

አውጪዎች የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በማዘጋጀት በባለሥልጣኑ የማይመዘገቡ ከሆነ እና በሂደት በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የማይመዘገቡ ከሆነ እየተደራጀ በሚገኘው የተማከለ ገበያ አርቲፊሻል ዋጋ እንዲፈጠር በማድረግ እና የጎንዮሽ ሃሰተኛ ገበያ በመፍጠር የተማከለ ገበያውን ተዓማኒነት ሊሸረሽር ይችላል። ስለዚህ ነባርም ሆነ አዲስ የሚወጡ የድርሻም ሆኑ የእዳ ሰነዶችን ለሦስተኛ ወገን ከመተላለፋቸው በፊት በተቀመጠላቸው የምዝገባ መፈርቶች መሠረት አውጪዎቹ በባለስልጣኑ እና በሂደት በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መመዝገባቸው የሰነዶቹን ትክክለኛ ዋጋ በመወሰን ረገድ የማይተካ ሚና ይጫወታል።

በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 75(4)(ሀ-ሠ) የተዘረዘሩት ልዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ነባርም ሆነ አዲስ ለሕዝብ ሽያጭ የሚቀርቡ ሰነዶችን ማስመዝገብ ግዴታ ነው። በአዋጁ ልዩ ሁኔታዎች ተብለው የተቀመጡት በኢትዮጵያ መንግሥት ለሽያጭ በቀረቡ ሰነዶች፣ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በሚሸጡ ሰነዶች፣ መክሰራቸዉ የታወጀባቸዉ ኩባንያዎች ሰነዶች፣ በግል ለሽያጭ የሚቀርቡ ሰነዶች፣ እና ባለሥልጣኑ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ከምዝገባ ነፃ የሚደረጉ ሰነዶችን ያጠቃልላል።

***<u>የሕዝብ ኩባንያዎችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ እና የሚያስከትለው ውጤት</u>***

በመመሪያው እንደተመለከተው የሕዝብ ኩባንያ ማለት አክሲዮን ማህበር ሆነው አክሲዮኖቻቸውን ከሃምሳ ሰው በላይ ሽያጭ ያወጡ ወይም የሸጡትን እንደሆነ ይደነግጋል። በተጨማሪም የሕዝብ ኩባንያ ማለት በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ ሰነዶቹን የሚሸጥ ድርጅት ማለት ነው። ሰነዶቹን ለሕዝብ ሽያጭ የሚያወጣ የሕዝብ ኩባንያ ከሁለቱ ገበያዎች ውጪ አክሲዮን መገበያየት የተከለከለ እንደሆነ የሚያመላክት ሲሆን በሁለቱ ገበያዎች ሰነዶቹን ለሕዝብ ለመሸጥ በቅድሚያ ከማስመዘገብ ውጪ ምንም ዓይነት አማራጭ እንደሌለው ለመረዳት ይቻላል። በዚህ አኳሃን አውጪው ሳይመዘገብም ሆነ ከተመዘገበ በኋላ ሰነዶቹን በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ውጪ መገበያየት የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው።

ከዚህ ጋር በቀጥታ የሚገናኘው የአዋጁ አንቀጽ 106(5) ሲሆን ማንኛውም ሰው ያልተመዘገበ፣ በመንግስት ዋስትና ያልተሰጠው ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት በወጣ መመሪያ ከምዝገባ መስፈርቶች ግዴታ ነፃ ያልሆነ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ያወጣ እንደሆነ፣ ከብር 150ሺ በማያንስና ከብር 300ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ7 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እንደሚቀጣ ተደንግጎ ይገኛል።

በሌላ በኩል ፈቃድ ከተሰጣቸው የግብይት ሥርዓቶች ውጪ ግብይት ማከናወን ክልክል መሆኑን እና የወንጀል ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል የአዋጁ አንቀጽ 106(3) ይደነግጋል። ማንኛውም ሰው ፈቃድ በሌለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ የሌለዉ መሆኑን እያወቀ የተገበያየ እንደሆነ፣ ከብር 100ሺ በማያንስና ከብር 150ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ5 ዓመት በማያንስና ከ12 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል። በአዋጁ አንቀጽ 2(18) መሠረት በሰነደ ሙዓለ ንዋይ መገበያየት ማለት ለራስ ወይም ለሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መሸጥ ወይም መግዛት፣ማውጣት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ፣ ማስቀመጥና መጠበቅ፣ ክፍያ ማጣራትና መፈጸም፣ ማበደር ወይም ማስያዝ፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ባለሥልጣኑ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ የሚደረግ ግብይት ነው ብሎ የሚወስነውን ሥራ ያካትታል። አክሲዮን ማህበር ሆነው የባለአክሲዮኖቻቸው ቁጥር ሃምሳ እና ከዛ በታች የሆኑትን ጨምሮ ምዝገባ አያስፈልጋቸውም ተብለው በአዋጁ እና በመመሪያው ከተጠቀሱት በስተቀር በአውጪዎች ለገበያ የቀረቡም ሆኑ አዲስ የሚወጡ ሰነዶች ሳይመዘገቡ በማናቸውም ዓይነት መገበያየት የተከለከለ መሆኑ በመመሪያው ተመልክቶ ይገኛል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የምዝገባ ሂደቱን የሚመሩት በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ባንኮች ወይም ኢንቨስትመንት አማካሪዎች ይሆናሉ።በተጨማሪ በሂደቱ የአንድን አውጪ የምዝገባ ሰነድ ለማዘጋጀት ኦዲተሮች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ የሀብት ግመታ ባለሙያዎች እንደ ሁኔታው ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት ሰጪዎችም ይሳተፋሉ። በዚህ ሂደት በደንበኛ ሳቢ መግለጫው እንደ ኦዲት ሪፖርት ያሉ ስራዎች ላይ ሃሰተኛ መረጃዎች ማካተት የወንጀል ሃላፊነትን ያስከትላል። በአዋጁ አንቀጽ 100 እንደተለመከተው ማንኛውም ሰው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ፣ ሌላ ሰው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም ሌሎች የተመዘገቡ ማናቸውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት ቃል እንዲገባ፣ እንዲገዛ፣ ወይም እንዲሸጥ ለመገፋፋት አላማ፤ ወይም የሰነደ

ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ ባለበት እንዲቀጥል፣ እንዲጨምር፣ እንዲቀንስ ወይም እንዲረጋጋ ለማድረግ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ መስጠት እንደሌለበት ይህን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከብር 200ሺ በማያንስና ከብር 350ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ7 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እንደሚቀጣ ይደነግጋል።

በአውጪው ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ሂደት ከባለሥልጣኑ የሚወሰኑ ማንኛውም አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እና አለመግባባቶች በይግባኝ ወደ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚቻል እና ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በህግ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ ማሳለፍ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 64 እና ተከታዮቹ ተደንግጎ ይገኛል።

በባለሥልጣኑ የሚደረግ የአውጪዎች ሰነድ ምዝገባ ግልጸኝነትን ከማስፈን ባሻገር ኩባንያዎች ስለድርጅታቸው ትክክለኛ ቁመና ለሕዝብ ይፋ በማውጣት እና አክሲዮን ወይም ቦንድ በመሸጥ በካፒታል ገበያ በኩል ከሕዝብ ገንዘብ የሚሰበስቡበት፣ ገዥዎችም የሚፈልጉትን ድርጅት አክሲዮን ሲገዙ ስለሚገዙት ድርጅት አክሲዮን ሙሉ መረጃ ኖሯቸው እንዲገዙ፣ ገንዘባቸው እንዳይበላ እና ኪሳራ እንዳይደርስባቸው ለማድረግ ይረዳል። አውጪዎች ስለድርጅታቸው ዝርዝር እና እውነተኛ መረጃ ለሕዝብ ይፋ የሚያወጡ እና በባለሥልጣኑ የሚመዘገቡ መሆኑ ከሕዝቡ ዘንድ የበለጠ ተዓማኒነት እና ተመራጭነት እንዲያገኙ በማድረግ ራሳቸውን በየጊዜው እንዲፈትሹ እድል በመስጠት የስጋት አስተዳደር እንዲኖራቸው እና ለኪሳራ እንዳይዳረጉ ትልቅ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይገመታል። በተጨማሪ ምዝገባው ለገበያው ታዓማኒነት በመፍጠር በሃገራችን በትክክል የሚሰራ የካፒታል ገበያ እንዲኖር በማድረግ ዘርፉ ለኢኮኖሚው እድገት ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት የራሱን አስተዋጾ ያበረክታል።

ስለዚህ ሰነዶችን ለሕዝብ ሽያጭ በሚያወጣው ድርጅት በኩል ተገቢው መግለጫ ተዘጋጅቶ ቅድሚያ በባለሥልጣኑ ማስመዝገብ እና ማስጸደቅ የሕግ ግዴታ ሲሆን የተለያዩ ሃሰተኛ ማማለያዎችን በሚጠቀሙ አክሲዮን ሻጮች እና የአክሲዮን ግብይቶች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ለመጠቆም እንወዳለን።